# የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

**ጥር 2011 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

ማውጫ


1. 1.አጭር ማጠቃለያ 2
2. 2.የዝግጅት ምዕራፍ፡ 3
3. 3.የ2011 በጀት ዓመትየግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት 4

3.1. የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ፡- 4

3.2. ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለን መስተጋብር ማጎልበት 5

3.3. የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድ ማሳደግ 6

3.3.1. ወጪ ቆጣቢነትንና ውጤታማነትን ማሻሻል፤ 6

3.3.2. የክልሎችና ጤና ተቋማት የመድሃኒት በጀት አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት፤ 9

3.3.3. የመድኃኒት ብክነት መቀነሻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ፤ 10

3.3.4. የመድሃኒት ዋጋ ትመና ማጠናከር፤ 11

3.3.5. ገበያ ጥናት በማከናወን ገበያውን ማረጋጋት፣ 11

3.4. የመድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን ማጎልበት 12

3.4.1. ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ማጠናከር 12

3.4.2. የግዥ ጨረታ አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር፤ 13

3.4.3. የሀገር ውስጥ አምራቾች አፈጻጸም 14

3.4.4. የኮንትራት አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር፤ 15

3.4.5. የመጋዘን አያያዝና የክምችት አስተዳደር ሥርዓት ማጠናከር፤ 16

3.4.6. የስርጭት እና ተሽከርካሪዎች ስምሪት አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር፤ 18

3.5. ስ.ግ. አ.ግ. ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት 19

3.5.1. የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ማጎልበት፤ 19

3.5.2. የአቅርቦት ሰንሰለት መሠረተ ልማት ማጎልበት፤ 20

3.5.3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ፈጠራን ማጎልበት፤ 20

3.5.5.1. የመልካም አስተዳደር እና ስነምግባር አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣ 21

3.5.5.2. የህግ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣ 22

3.5.5.4. የጠቅላላ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣ 23

3.5.5.5. ስርዓተ ጾታ እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ አገልግሎት ማጠናከር፣ 24

4. 4.የበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት የፋይናንስ አጠቃቀም፤ 25
5. 5.በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ስራ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች 26
6. አባሪ 1፡ የቁልፍ አፈጻጸም መለኪያዎች (KPIs) ያሉበት ደረጃ ማጠቃለያ 28

## 1. አጭር ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ እየተተገበረ የሚገኘውን የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የግማሽ ዘመን አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ ዕቅዱን ከልሶ አዘጋጅቷል፡፡ስትራቴጂክ ግቦቹን ለክትትልና ግምገማ በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ከተከለሰው ስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀዳ ሲሆን እንደ ፍላግሺፕ ስትራቴጂክ እርምጃ የህይወት አድን መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን 95% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

ከዚህ ሌላ የዕቅድ አፈጻጸሙን ለመከታተል የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የአፈጻጸም መለኪያዎችን በኤጀንሲ ደረጃ (Corporate level KPIs)፣ በስራ ሂደት ደረጃ (Process level KPIs) እና በፈጻሚ ደረጃ (individual level KPIs) ተዘጋጅተው የመረጃ መሰብሰቢያና ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾች ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፉ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፎች ተግባራዊ መደረግ ተጀምሯል፡፡

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት የተለካ ሲሆን ውጤቱም የጤና ፕሮግራም የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ትንበያ ትክክለኛነት በአማካይ 80.2% ሲሆን በተገላባጭ ፈንድ ተገዝተው የሚቀርቡ መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት ደግሞ 66.1% ማድረስ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት የህይወት አድን መድሃኒቶች አቅርቦት 74.8% ማድረስ ተችሏል፡፡ በስድስት ወር ውስጥ የነበረው የበጀት አጠቃቀም 98% ነው፡፡

## 2. የዝግጅት ምዕራፍ፡

የኤጀንሲውን የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ለመገምገም ከባለድርሻ አካላት ጋር የ3 ቀናት የግምገማ መድረክ በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡ በግምገማ መድረኩ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከሆስፒታሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተሳተፉበት ተካሂዷል፡፡ በመድረኩ ላይም የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና 2011 በጀት ዓመት አንኳር ዕቅድ ቀርበው ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ተሳታፊዎቹ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱና ዕቅዱ ላይ የቡድን ውይይት አድርገዋል፡፡ የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በየደረጃው በማካሄድ በግምገማ መድረኩ የተገኙ ጭብጦች ለ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ኤጀንሲውን በበለጠ ሊገልጹና ሊለኩ የሚችሉ ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ ግቦች ተቀርጸዋል፡፡ እነዚህን የኤጀንሲው ስትራጂክ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ ግቦች በየደረጃው የሚገኝ አመራር እንዲረዳው በማድረግ የኤጀንሲውና የስራ ክፍሎች ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም ለፈጻሚዎች ኦሬንቴሽን ተሰጥቶ ዕቅዱ በየደረጃው ከወረደ በኂላ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ዕቅዱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ተልኳል፡፡

ኤጀንሲው ገዝቶ የሚያቀርባቸውን መድኃኒቶች፣ የሕክምና መገልገያዎች፣ የላቦራቶሪ ኬሚካልና ሪኤጀንቶች እንዲሁም የሕክምና መሳሪያዎች የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በተገላባጭ ፈንድ 1,272 መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎችን እንዲሁም በጤና ፕሮግራም 101 መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎችን በጥቅሉ 1,373 መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ተለይተው የኤጀንሲው የግዥ መዘርዝር የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ 5,000 ኮፒ በማሳተም በይፋ ተመርቋል፡፡

የክትትልና ግምገማ የስልጠና ማኑዋል ተዘጋጅቶ የአሰልጣኞች ስልጠና በሁለት ዙር ከሁሉም ቅርንጫፍ ለተውጣጡ 124 አስተባባሪዎች ተሰጥቷል፡፡ የኤጀንሲው የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡ የኤጀንሲውን፣ የስራ ክፍሎችንና ፈጻሚዎችን ለመለካት የሚያስችሉ ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች በማዕቀፉ ተካተዋል፡፡ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፉ ኤጀንሲው ባዘጋጀው ዓመታዊ የግምገማ መድረክ ላይ በይፋ ተመርቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

## 3. የ2011 በጀት ዓመት የስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የ2011 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በቁልፍና አበይት ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1. የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ፡-

በኤጀንሲው 162 የኬዝ ቲም ፎረሞች ያሉ ሲሆን በዋና መ/ቤት 40 ኪዝ ቲም ፎረም እና በቅርንጫፍ ደረጃ 122 ኬዝ ቲሞች ተደራጅቷል፡፡ በዋና መ/ቤት የኬዝ ቲም ፎረሞች ግንኙነት በተመለከተ እና ውይይቶችን ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ ከማካሄድ አንጻር አንድ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴው የኤጀንሲውን ግቦች ከማሳካት አንጻር ስራዎችን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ እንዲሰሩ በማድረግ፣ በአፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እየተወያዩ መፍትሔ በመስጠትና የጋራ የመማማሪያ መድረክ ከመፍጠር አኳያ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ ሲሆን አሁንም ሂደቱ ላይ በተወሰነ መልኩ መቆራረጥ ያለበት መሆኑ ተገምግሟል፡፡

### 3.2. ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለን መስተጋብር ማጎልበት

#### የስትራቴጂክ እርምጃዎች አፈጻጸም

8772 ነጻ የስልክ መስመርን ወደ ዲጅታል E1 በመቀየር እንዲሁም ዞይፐር የተባለ ሶፍትዌር በመጠቀም በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት ሰዎች ብቻ ሲያስተናግድ የነበረውን ተጨማሪ 30 መስመሮች በመጨመር ተደራሽነቱን የማስፋት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የነጻ የስልክ መስመሩን አጭር የጽሁፍ መልዕክት ለማስተላለፍ እንዲቻል መስመሩ ተዘርግቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ሶፍትዌር የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በነጻ የስልክ መስመሩ በዚህ ግማሽ ዓመት ከተለያዩ ጤና ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች 111 ጥቆማዎች የደረሱ ሲሆን በአግባቡ ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፋኖስ ዳሽ ቦርድ ሁሉም የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም ሌሎች ተጠቃሚዎች በኤጀንሲው የሚገኙትን መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዚህም በኤጀንሲው የፌስቡክ ገጽ ላይ ሊንክ በመጫን የመድሃኒቶች አቅርቦት መረጃዎችን ለተገልጋዮች ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን መድሃኒት ስም በማስገባት የሚፈልጉት መድሃኒት የት ቅርንጫፍ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ የሚችሉበት አሰራር ተፈጥሯል፡፡

የህብረተሰቡን የመድሃኒት ፍላጎት እውን ለማድረግ ከቅርንጫፎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት ለማጠናከር የ22 ሆስፒታሎች ኢኒሼቲቭ በአዲስ አበባ ቁጥር 1 እና 2 ቅርንጫፎች በመተግበር የሆስፒታሎችን የክምችት መጠን ከ95% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ በኤጀንሲ በየደረጃው ያለውን የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት በማጠናከር እንዲሁም አግባብ ያለው የግብረ መልስ አሰጣጥ ስርዓት በማጎልበት የክምችትና ስርጭት ስርዓቱን በማሻሻል በክምችት ያሉ መድሃኒቶች በተገቢው ሁኔታ ለህብረተሰቡ ማድረስ ያስችል ዘንድ አዳዲስ ወደ ክምችት የሚገቡ መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎችን በማህበራዊ ሚዲያ (ቫይበር) ማሳወቅ ተጀምሯል፡፡

ሰላሳ ሶስት ስፔሻላይዝድና ከፍተኛ የታካሚ ብዛት ያላቸውን ሆስፒታሎች በመለየት የክምችት ክትትል ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ በመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች አቅርቦት ዙሪያ ከአምራቾችና ወኪሎች ጋር የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በውይይቱ ወቅት የተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችንም የአፈጻጸም መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለመፍታት እየተሰራ ይገኛል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያ፡-**

KPI1: **የጤና ተቋማት እርካታ ወደ 80% ማድረስ- በዓመት የሚለካ**

### 3.3. የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድ ማሳደግ

## ስትራቴጂክ እርምጃዎች

### 3.3.1. ወጪ ቆጣቢነትንና ውጤታማነትን ማሻሻል፤

በበጀት ዓመቱ ወጪ በመቆጠብ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሰረት በርካታ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እና አሰራር ለመዘርጋት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ጊዜን እና ወጪን ለመቆጠብ በተዘረጋው አሰራር መሰረት በባህር ተጭነው የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ሞጆ ደረቅ ወደብ ከደረሱ በኂላ በ48 ቀናት ውስጥ ማንሳት የተቻለ ሲሆን በአየር ተጭነው የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ደግሞ በ17 ቀናት ውስጥ ማንሳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የተከማቸ የኮንቴነር ኢንተርቸንጆችንም ለመመለስ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የ2011 በጀት ዓመት የኮንቴነር ኢንተርቸንጆችን በ10 ቀናት ውስጥ ለመመለስ ተችሏል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀርቡ ያልቻሉና ወደፊትም መቅረብ የማይችሉ የብር 12,243,909 ዋጋ ያላቸው 19 የግዥ ትዕዛዞችን በመለየት እንዲሰረዙ በማድረግ ገንዘቡን ለሌላ የግዥ ትዕዛዞች ማዋል ተችሏል፡፡

**ሒሳብ መዝጋት እና የኦዲት ስራ፡**

ወጪን ከሚቀንሱ አሰራሮች ውስጥ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እና ተከታታይ የኦዲት ስራ በማካሄድ በውጤቱ መሰረት የማስተካካያ እርምጃ መውሰድ ይገኙባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በስድስት ወራት ውስጥ የሚከተሉት ስራዎች ተከናውነዋል፡-

**በውስጥ ኦዲት የተከናወኑ ተግባራት**

1. የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ቀጥር አንድ የ2009 በጀት ዓመት ጉድለት እና ብልጫ የውስጥ ኦዲት በመካሄድ ላይ ነው፡፡ የነገሌ ቦረና የ2009 በጀት ዓመት ጉድለት እና ብልጫ የውስጥ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

2. የዋናው መ/ቤት ከሐምሌ 1 ቀን 2010 እስከ ህዳር 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ያለው የመድሃኒት ክምችት ወጪ ማረጋገጫ (Dispatch confirmation) እና የጤና ተቋማት የክምችት ርክክብ ማረጋገጫ የውስጥ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
3. በአዲስ አበባ ቁ.1 ቅርንጫፍ በተመረጡ መድኃኒቶች ላይ መድኃኒቶቹ ለሆስፒታሎች (የካቲት 12 እና ራስ ደስታ ዳምጠው) ገቢ መሆናቸውን የገቢ የውስጥ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
4. የባህርዳር ቅርንጫፍ ከሐምሌ 1 ቀን 2010 እስከ መስከረም 30 ቀን 2011 የመድሃኒት ክምችት መጋዘኖች የክምችት ወጪ ማረጋገጫ (Dispatch confirmation) እና የጤና ተቋማት የክምችት ርክክብ ማረጋገጫ (ሞዴል-19 confirmation) ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
5. የነገሌ ቦረና ቅርንጫፍ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመቶች የተመረጡ ደረሰኞች ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖረት ቀርቧል፡፡
6. የዋና መስሪያ ቤት ቃሊቲ ቁጥር 2 መጋዘን የ2010 በጀት ዓመት የተገላባጭ ፈንድ እና የፕሮግራም መድኃኒቶች ጉድለት አና ብልጫ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
7. የዋና መስሪያ ቤት የለቡ 1 መጋዘን የ2010 በጀት ዓመት የተገላባጭ ፈንድ እና የፕሮግራም መድኃኒቶች ጉድለት እና ብልጫ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

<u>በውጭ ኦዲት የተከናወኑ</u>

ባለፉት ዓመታት የኤጀንሲው ሂሳብ በፋይናንስ አዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አለመዘጋት፣ ኦዲት አለማስደረግ እና በሚሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት፡

1. የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተጠናቅቆ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡
2. የ2009 በጀት አመት የሂሳብ መግለጫ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ሪፖርቱ ለኦዲት ስራ ለኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ተልኳል፡፡
3. የ2010 በጀት ዓመት ጥራቱን የጠበቀ የሂብ ሪፖርት እየተዘጋጀ ነው፡፡
4. በመንግስት ግዥ ኤጀንሲ አማካኝነት የተደረገውን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኦዲት እንዲሁም በፌደራል ዋና ኦዲተር አማካኝነት በኤጀንሲው ግንባታዎች ላይ

የተከናወነውን የክዋኔ ኦዲት ተከትሎ በተገኙት ውጤቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ ሲሆን አፈጻጸሙም በየጊዜው ክትትል እየተደረገበት ነው።

## የፋይናንስ ውስጣዊ አሰራር ለማጠናከር የተከናወኑ ተግባራት

የሞዴል 19 የአሰባሰብ ስርዓቱን በማጠናከር ወጥ የሆነ ፎርማት አዘጋጅቶ በመላክ እና ሞዴል 19 በወቅቱ የማይሰጡትን ተቋማት በመለየት ሞዴል 19 በአግባቡና በወቅቱ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። በሲስተም እና በቆጠራ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥራት፤ ወቅቱን የጠበቀ የሂሳብ ልዩነትን የማስታረቅ ስራ ተሰርቷል። የ10 መጋዘኖች HCMIS እና ፊዚካል ቆጠራን የማሰታረቅ ስራ ተሰርቷል።
በቅርንጫፎችና ዋናው መስሪያ ቤት መካከል ያለውን የሂሳብ ልዩነት ለማጥበብ ግብረሀይል በማቋቋም የታዩ ልዩነቶችን የማስታረቅ ስራ ተሰርቷል።

የተገላባጭ ፈንድ መጠንን ለመጨመር የተከናወኑ ተግባራት፡

- ኤጀንሲው ቀደም ሲል የተጠናከረ የበጀት ስርዓት ያልነበረው ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት በጥናት ላይ የተመሰረተ በጀት እንዲዘጋጅ እና እያንዳንዱ ስራ የተያዘለትን በጀት ተከትሎ እንዲፈጸም እየተደረገ ነው።
- የተመደበውን በጀት ለመከታተል እንዲቻል እና ወጪ የሚያንሩ አሰራሮች እና የስራ ክፍሎች በመለየት ማስተካከያ እርምት መውሰድ እንዲቻል Management Accounting Team በማቋቋም የተጠናከረ ስራ እየተሰራ ነው።
- የተገላባጭ ፈንድን ለመቆጠብ ብሎም ለማሳደግ እንዲቻል ስልጠናዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ከመደረጉም በላይ አብዛኛዎቹ ስልጠናዎች በአጋር ድርጅቶች እንዲሸፈኑ ተደርጓል።
- በበጀት ዓመቱ የግዥ ፍላጎት በመቀነስ ኤጀንሲው ባለው ንብረት በአግባቡ እንዲጠቀም ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው።

### 3.3.2. የክልሎችና ጤና ተቋማት የመድሃኒት በጀት አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት፤

በ2011 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ ለጤና ተቋማት የዱቤ ሽያጭ ከሰጠው ብር 785,920,920.92 ውስጥ ብር 367,819,598.85 (47%) ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም በ2009 እና 2010 በጀት ዓመት ሳይሰበሰብ ከቀረውና እና ወደ 2011 በጀት ዓመት ከዞረው ከጤና ተቋማት ያልተሰበሰበ ብር 490,606,807.11 ውስጥ ብር 144,083,041.43 (29%) ተሰብስቧል፡፡ በጠቅላላው ብር 764,625,087.75 ተሰብሳቢ ሂሳብ ጤና ተቋማት ላይ ይገኛል፡፡

በየቅርንጫፉ ያለው የተሰብሳቢ ሂሳብ መጠን በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡

| ተ.ቁ | የቅርንጫፉ ስም | የተሰብሳቢ መጠን (በብር) |
|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ ቁጥር 1 | 466,641,451.77 |
| 2 | ባህርዳር | 75,452,447.00 |
| 3 | አዲስ አበባ ቁጥር 2 | 64,381,463.24 |
| 4 | ጂማ | 35,621,639.34 |
| 5 | መቐለ | 29,169,169.62 |
| 6 | ሐዋሳ | 21,944,330.68 |
| 7 | ባህርዳር | 21,381,826.00 |
| 8 | ጎንደር | 18,894,218.54 |
| 9 | ነቀምት | 13,353,393.16 |
| 10 | አዳማ | 12,443,089.24 |
| 11 | አርባምንጭ | 8,452,496.03 |
| 12 | ነገሌ ቦረና | 6,127,700.12 |
| 13 | ቀብሪዳር | 4,258,883.96 |
| 14 | ጋምቤላ | 2,916,518.38 |
| 15 | ሽሬ | 2,776,371.44 |
| 16 | አሶሳ | 1,834,254.92 |
| 17 | ሰመራ | 357,660.31 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **764,625,087.75** |

አዲስ አበባ ቁጥር አንድ ቅርንጫፍ በዱቤ ከሰጠው ብር 466,641,451.77 ውስጥ 309 ሚሊየን ብር የሚገኘው በጥቁር አንበሳና ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ነው፡፡

በተለያየ ጊዜ ጉዳት ደርሶባቸው ጥቅም ላይ መዋል ላልቻሉ መድሃኒቶች ኢንሹራንሲ ክሌይም ተጠይቆ ለተወሰኑ ክሌሞች ለኤጀንሲው ክፍያ ተፈጽሟል፡፡

ለጤና ተቋማት አገልግሎት ተሰጥቶ ከጤና ጥብቃና አጋር ድርጅቶች የአገልግሎት ክፍያ ተሰብስቧል፡፡ በስድስት ወሩ ገቢ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡-

በ2011 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዉስጥ የተወራረደ የግዥና የአገልግሎት ክፍያ

| S/N | ዝርዝር | ከዕቃዉ ዋጋ | የግዥ አገልግሎት ክፍያ | የክምችትና ስርጭት አገልግሎት ክፍያ | አጠቃለይ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2% | 5% | 7% |
| 1 | FMOH-MDG | 1,045,712,851.68 | 20,914,257.03 | 52,285,642.58 | 73,199,899.62 |
| 2 | FMOH-GF | 44,352,575.16 | 4,457,622.93 | 11,144,057.33 | 15,601,680.26 |
| 3 | GF-HAPCO | 1,011,278,622.57 | 20,225,572.56 | 50,563,931.37 | 70,789,503.93 |
| | Sub Total | **2,101,344,049.41** | **45,597,452.52** | **113,993,631.28** | **159,591,083.81** |

በተጨማሪም የብር 2,665,706,520.36 የግዢና ስርጭት አገልግሎት ለማከናወን ብር 139,954,892.88 የአገልግሎት ክፍያ ቅድምያ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

KPI2: የዱቤ ሽያጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሰብሰብ የሚወስደውን ጊዜ ወደ 60 ቀናት ማሳጠር-አፈጻጸም

KPI3: ከአጋር ድርጅቶች ክፍያ ለመሰብሰብ የሚወስደውን ጊዜ ወደ 7 ቀናት ማሳጠር---አፈጻጸም የግዢና አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ለመሰብሰብ 21 ቀናት የወሰደ ሲሆን በዓይነት ወደ መጋዘን ገብተው የክምችትና ስርጭት አገልግሎት ለሰጠናቸው ክፍያ ለመሰብሰብ 60 ቀናት ወስዷል

### 3.3.3. የመድኃኒት ብክነት መቀነሻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ፤

የክምችት አስተዳደር ስርዓቱን በማሻሻል በየደረጃው ያለውን የመድሃኒት ብክነት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ፤ የመጋዘን አስተዳደር ስርዓቱን በማሻሻል በከፍተኛ ወጪ ኤጀንሲው የተከራያቸውን መጋዘኖች ቁጥር መቀነስን እና የክምችት አስተዳደሩን በማጠናከር ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ

ክምችቶችን በማዘዋወርና ክምችት የማገላበጥ ሂደቱን በማፋጠን እንዲሁም በማዕከል በብዛት የተከማቹ መድሃኒቶችንና ህክምና መገልገያዎችን ወደ ቅርንጫፍ በአደራ መልክ (Consignment) በማዘዋወር የክምችት ወጪዎችን ለመቀነስ ታቅዶ 1,438 መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች በመለየት የብር 35,955,554.72 ዋጋ ያላቸው 935 መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች በማዘዋወር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

### 3.3.4. የመድሃኒት ዋጋ ትመና ማጠናከር፤

በስራ አመራር ቦርድ የጸደቁትን የመድሃኒቶች፣ የህክምና ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች የዋጋ አተማመን እና የፈንድ አስተዳደር መመሪያዎች ተግባራዊ በመደረጋቸው የዋጋ አወጣጥ እና የክፍያ ስርዓቱ ቀልጣፋ እንዲሆን ተደርጓል:: የ2011 በጀት ዓመት ስራ ለመጀመር የመድሃኒት ዋጋ የመትከል ስራ ተከናውኗል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI4:** ለመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ዋጋ ለመትከል የሚፈጀውን ጊዜ /Average Time from GRNF to Cost set date (IGRV-GRV) ወደ 1 ቀን ማሳጠር - አፈጻጸም 1 ቀን

### 3.3.5. ገበያ ጥናት በማከናወን ገበያውን ማረጋጋት፣

የአቅርቦት ፍላጎትን ለማሟላት የትንበያ ስርዓቱና የገበያ ጥናት አቅማችንን ማጎልበት መሰረት በማድረግ በግዥ ትንበያና ገበያ ጥናት ዳይሬክቶሬት ስር የገበያ ጥናት ቡድን ለማዋቀር ከፍተኛ ስራ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ ተጠናቆ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI5:** የተገላባጭ ፈንድ የገንዘብ መጠንን በ10% መጨመር -- የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

**KPI6:** በወቅቱ ሥራ ላይ የዋለና የተወራረደ የጤና ፕሮግራሞች ፈንድ - አፈፃፀም 100%

**KPI7:** Cash to cash cycle time (in months) ወደ 12 ወር ማሳጠር - የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

**KPI8:** የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች የብክነት መጠን ከ2% በታች ማድረስ - አፈፃፀም 0.65%

**KPI9:** የውስጥ አሰራርን በማሻሻል የተቀነሰ ወጪ - የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

**KPI10:** የፋይናንስ ሪፖርቶች ወቅታዊነት 100% ማድረስ /Financial reporting timelines/-- አፈፃፀም - 100%

## 3.4. የመድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን ማጎልበት

### ስትራቴጂክ እርምጃዎች እና አፈጻጸማቸው

### 3.4.1. ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ማጠናከር

ለቅርንጫፎች የመድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ክምችት አያያዝና ስርዓት ሂደት የሚገልፅ የክምችት ትንተና (ABC & VEN analysis) ለማዘጋጀት ስልጠና ተሰጥቶ የትንተና ቅፅ የተሰራጨ ሲሆን አዲስ አበባ፣ መቀሌ፣ ሐዋሳ፣ አዳማ፣ ባህር ዳር፣ ጅማ ቅርንጫፎች የክምችት ትንተና አዘጋጅተዋል፡፡ የተቀሩት ቅርንጫፎች ትንተናውን እንዲሰሩ ክትትል በመደረግ ላይ ነው፡፡ ህይወት አድን መድሃኒቶች በየወሩ በኤጀንሲዉ መጋዘኖች (በዋና መ/ቤትና ቅርንጫፎች) ያለ፣ በግዥ እና ትራንዚት ሂደት ያለውን ክምችት ልየታ በማድረግ ከወቅታዊ ፍጆታ ጋር በማነፃፀር የክምችት ይዘት ሪፖርት ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት ስድስት ወር ላይ የነበረው የህይወት አድን መድሃኒቶች አቅርቦት 74.8% ነው፡፡

በተገላባጭ ፈንድ ተገዝተው የሚቀርቡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ለማጠናከር የኤጀንሲውን ግዢ መዘርዝር መነሻ በማድረግ ለ2011 በጀት ዓመት የትንበያ ቅፅ ተዘጋጅቶ ቅጹን ለቅርንጫፎች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ የኤች.አይ.ቪ ሬጂመን ዳታን ለመሰብሰብ የሚያስችል ቅፅ ተዘጋጅቷል፡፡ የቲቢና ወባ ግብአቶች የግዢ ትንበያና ክለሳ ተሰርቷል፡፡ ለቤተሰብ ምጣኔ፣ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ፣ ወባ፣ እናቶችና ሕፃናት ጤና ግብዓቶች ላይ የአቅርቦት ዕቅድ ክለሳ ተሰርቷል፡፡

በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ፣ ቲቢ፣ ወባ እንዲሁም የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራሞች ላይ በተመረጡ መድኃኒቶች ላይ የትንበያ ትክክለኛነት (Forecast Accuracy) የተሰራ ሲሆን ለጤና ፕሮግራም መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት

በአማካኝ 80.2% ሲሆን ለተመረጡ በተገላባጭ ፈንድ ተገዝተው የሚቀርቡ መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት ደግሞ 66.1% ነው፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

KPI11: የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ትንበያ ትክክለኛነት አሁን ካለበት ከ75% በላይ ማሳደግ፣ - አፈጻጸም- በጤና ፕሮግራም 80.2%፣ በመደበኛ በጀት 66.1%

KPI12: የህይወት አድንና መሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦትን ከ69% ወደ 95% ማድረስ፤ - አፈጻጸም- የመደበኛ ህይወት አድን መድሃኒቶች አቅርቦት 74.8%፣

### 3.4.2. የግዥ ጨረታ አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር፤

ከጤና ተቋማት ለሚቀርቡ የሕክምና መሳሪያዎች የግዢ ጥያቄ ግምታዊ ዋጋ እንዲሁም የቴክኒክ መስፈርት (specification) የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከቀረቡት የግዢ ጥያቄዎች ውስጥም በኤጀንሲው የግዢ መዘርዝር ውስጥ የሌሉት የሕክምና መሳሪያዎችን ተቋማት እንዲያውቋቸው ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ችግር ላጋጠማቸው የሕክምና መሳሪያዎች የመለዋወጫ ግዢ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ጤና ተቋማት፣ ዩንቨርስቲዎች እና ድርጅቶች የህክምና መሳሪያ እንዲቀርብላቸው 138 ውል የገቡ ሲሆን በገቡት ውል መሰረት ቅድመ ክፍያ መክፈላቸውን የህክምና መሳሪያው መሰራጨቱን እና መሳሪያው ከተሰራጨላቸው ተቋማት ቀሪ ገንዘብ መሰብሰቡን በማጣራት ያልተሰበሰቡትን በመለየት ገንዘቡ ገቢ እንዲሆን እየተሰራ ሲሆን የህክምና መሳሪያ ላልቀረበላቸው ተቋማት ደግሞ ግዥ እየተከናወነ ነው፡፡

ለ2011 የሚያስፈልጉ የፕሮግራምና የመደበኛ መድኃኒቶች፣ የህክምና መገልገያዎችና ኬሚካሎች ግዥ የተጠናቀቀ ሲሆን በዚሁ መሰረት ተገቢውን የጨረታ ዘዴ በመጠቀም በስድስት ወሩ በመደበኛ በጀት የብር 3,528,394,560.84 ዋጋ ያላቸው እንዲሁም በጤና ፕሮግራም የብር 2,843,358,493.35 ዋጋ ያላቸው በድምሩ የብር 6,371,753,054.19 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የግዥ ትዕዛዝ ይዘዋል፡፡

በኤጀንሲው የሚከናወኑ ግዥዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲጠናቀቁ የቅድመ ግዥ አስተዳደር ስርዓትን በመከታተል የግዥ ጥያቄዎች በመጡበት ቅፅበት የጨረታውን ዘዴ በመወሰን የግዥ ፍቃድ እንዲጠየቅና የተጠየቀው የግዥ ፍቃድን በመከታተል፣ እንዲሁም ለተፈቀዱ የግዥ ጥያቄዎች የጨረታ ሰነድ መዘጋጀቱንና ሌሎች አስፈላጊ ሂደቶች

መሟላታቸውን በመከታተል የሚወስደውን ጊዜ መቀነስ ተችሏል፡፡ የድህረ ምዘና ሂደቱን በመከታተልና አስፈላጊውን የግንኙነት መረብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመፍጠር አስፈላጊ መረጃዎችን በተፈለገው የጊዜ ገደብ እንዲያመጡ ማድረግ ተችሏል፡፡
የጨረታ ምዘና ጊዜን መቀነስ የሚያስችለው ዋንኛው መንገድ ግዥዎችን በማዕቀፍ ስምምነት መፈጸም ሲሆን በስድስት ወሩ ለሶስት ዓመት አገልግሎት የሚውል 26 የጸረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች የግምገማ ሂደት ተጠናቋል፡፡ ለሶስት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የሄማቶሎጂ፣ ኬሚስትሪ እና የስኳር መመርመርያ ማሽኖች በቅያሪ የማዕቀፍ ግዢ (placemenet tender) ተከናውኖ የ3 ዓመት የረጅም ጊዜ የግዢ ፍሬምዎርክ ስምምነት ተፈጽሟል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

KPI13: የግዢ ጥያቄ ከቀረበበት የግዥ ትዕዛዝ እስከሚይዝበት ያለውን ቀን ወደ 90 ቀን ማድረስ- በቀጥታ ግዢ 91 ቀናት ሲሆን በግልጽ ጨረታ ደግሞ 107 ቀናት ይወስዳል

KPI14: የግዢ ትዕዛዝ ከያዘበት እስከ ኮንትራት የሚፈረምበት ያለውን ቀን ወደ 15 ቀን ማሳጠር- አፈጻጸም 27.6 ቀናት

KPI15: የግዥ ሂደት የሚወስደውን ቀን አሁን ካለበት 280 ቀን ወደ 160 ቀን ማሳጠር -- የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

### 3.4.3. የሀገር ውስጥ አምራቾች አፈጻጸም

የሀገር ውስጥ አምራቾች አቅም ለማጠናከርና በመንግስት የተያዘውን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ ለሃገር ውስጥ አምራች 25% የዋጋ ከለላ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው አምራቾች የውሉን 30 ፐርሰንት ቅድመ ክፍያ በመስጠት እንዲበረታቱ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታዎች ላይ በመሳተፍ ከአጠቃላይ የግዥ ትዕዛዝ ውስጥ ብር 1,276,193,103.26 የሚሆነው ለሀገር ውስጥ አምራቾች የተሰጠ ነው፡፡
የአገር ውስጥ አምራቾች በስድስት ወር ውስጥ ከተሰጣቸው የብር 886,557,227.48 ዋጋ ያለው ውል ውስጥ የብር 231,913,060.88 (26.2%) ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች አቅርበዋል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸማቸው በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡

**የ2011 በጀት ዓመት የግማሽ አመት የአገር ውስጥ አምራቾች አቅርቦት አፈፃፀም በብር**

| ተ.ቁ | የአምራች ስም | ለስድስት ወሩ የተሰጠ ውል (በብር) | በስድስት ወሩ የቀረበ መጠን (በብር) | በስድስት ወር የቀረበው በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ መድሃኒት ፋብሪካ | 319,593,957.77 | 107,880,453.10 | 33.8% |
| 2 | ኢትዮጲያ መድሃኒት ፋብሪካ | 269,937,087.90 | 80,912,575.31 | 30.0% |
| 3 | ካዲላ መድሃኒት ፋብሪካ | 65,605,135.32 | 20,699,031.56 | 31.6% |
| 4 | ጁልፋር መድሃኒት ፋብሪካ | 16,226,459.46 | 8,018,753.86 | 49.4% |
| 6 | ሳንሼንግ መድሃኒት ፋብሪካ | 189,339,823.49 | 7,936,432.71 | 4.2% |
| 5 | ኢስት አፍሪካ መድሃኒት ፋብሪካ | 25,527,958.61 | 6,139,009.40 | 24.0% |
| 7 | ፈውስ መድሃኒት ፋብሪካ | 326,804.94 | 326,804.94 | 100.0% |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **886,557,227.48** | **231,913,060.88** | **26.2%** |

### 3.4.4. የኮንትራት አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር፤

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ወደ መጋዘን የገቡ መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ. | በጀት | ወደ መጋዘን የገቡ ጠቅላላ ዋጋ በብር |
|---|---|---|
| 1 | በመደበኛ በጀት ተገዝተው ወደ መጋዘን የገቡ | 1,196,686,531.17 |
| 2 | በጤና ፕሮግራም (GF, SDG) | 989,936,502.58 |
| 3 | ከእርዳታ (MOH, Unicef እና Others) | 2,146,122,338.15 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **4,332,745,371.89** |

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ከብሔራዊ ባንክ ከGF&SDG የባንክ አካውንት 65,389,562 ዶላር ዋጋ ያላቸው የግዢ ትዕዛዞች LC/CAD በወቅቱ ተከፍቶላቸዋል፡፡ በመደበኛ በጀት ከኤጀንሲው የውጭ ምንዛሬ አካውንት 4,295,023.05 ዶላር ዋጋ ያላቸው የግዢ ትእዛዞች

LC/CAD የተከፈተላቸው ሲሆን መድሃኒቶቹና የህክምና መገልገያዎች እየገቡ ይገኛል፡፡ በስድስት ወሩ ለሚከናወኑ ግዢዎች 148,009,431 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ከብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ 83,000,000 (56%) ዶላር ተፈቅዷል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI16:** ለመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዢ LC/CAD ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ወደብ ላይ እስከደረሰበት ያለውን ጊዜ ወደ 90 ቀናት ማድረስ/Supplier lead time variability/ አፈጻጸም በባህር ተጭነው ለሚመጡ መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች 76 ቀናት የወሰደ ሲሆን በአየር ተጭነው ለሚመጡ ደግሞ 83 ቀናት ፈጅቷል

**KPI17:** መድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዢ ወደብ ላይ ከደረሰበት ቀን አንስቶ ወደ ኤጀንሲው መጋዘኖች ገቢ የተደረገበትን ከ25 ቀናት በታች ማድረስ- አፈጻጸም በባህር ተጭነው የሚመጡትን በ48 ቀናት እንዲሁም በአየር ተጭነው የሚመጡትን በ17 ቀናት ወደ መጋዘን ማስገባት ተችሏል

**KPI18:** አቅራቢዎች በውሉ መሰረት ማቅረብ የሚገባቸውን ያቀረቡበት መጠን /Supplier fill rate/- አፈጻጸም

### 3.4.5. የመጋዘን አያያዝና የክምችት አስተዳደር ሥርዓት ማጠናከር፤

ኤጀንሲው የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን ለማጎልበት እንዲያስችለው ከዚህ በፊት በሁለት ተከፍለው የነበሩትን የኤጀንሲው መጋዘኖች ወደ አንድ የመጋዘን አስተዳደር ስርዓት እንዲመጡ የተደረገ ሲሆን የመጋዘን ወለል ጥገና ስራ በባህርዳር፣ አዳማ እና መቐለ ቅርንጫፎች ተጠናቋል፡፡ የመጋዘኖች CCTV፣ Door Intrusion፣ Smoke Detection and Protection ተከላ በ8 ቅርንጫፎች የተጠናቀቀ ሲሆን በ8 ቅርጫፎች ደግሞ የተከላ ስራው ተጀምሯል፡፡ የአዳማ ቅርንጫፍ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ማስወገጃ ኢንሲኔሬተር ግንባታና ተከላ ተጠናቆ የሙከራ ስራ የተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የክምችትና ስርጭት አስተዳደርን አፈጻጸም ለማሻሻል ቁልፍ መለኪያ ተብሎ ከተለየውና ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው አንዱ የቆጠራ ትክክለኛነትን ማሻሻል ነው፡፡ ይህም በቆጠራ የሚገኝ ውጤት ቢን ካርድ ላይ ከሚጻፈው ጋር ተመሳሳይ

መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት በዋና መስሪያ ቤት መጋዘኖች በተካሄደ የክምችት ትክክለኛነት ዳሰሳ የቆጠራ ትክክለኛነት 80% ነው፡፡

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የክምችት ትክክለኛነትን ለመጨመር በዋናው መስሪያ ቤት በየዕለቱ 120 ፓሌት በመቆጠር ላይ ሲሆን በሚገኘው ውጤት መሰረትም የማስተካከያ እርምጃዎች በየዕለቱ ተወስደዋል፡፡ የመጋዘን አያያዝን ለማሻሻል በየሳምንቱ የGDP (Good Distribution Practice, Warehouse, yard cleanless and cold room) ምዘና እየተሰራ ይገኛል፡፡ የክምችት አስተዳደርን ለማጠናከር የABC/FNSD እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህ ትንተና ሲያልቅ በዋናው መስሪያ ቤት ግቢ ያሉ መጋዘኖች ፈጣን እንቅስቃሴ ያላቸው መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች የሚከማቹባቸው እና ሌሎች መጋዘኖች ደግሞ አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የሚከማቹባቸው ይሆናል፡፡

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በኤጀንሲው መጋዘኖች ውስጥ የብር 2,036,092,212.06 ዋጋ ያላቸው የመደበኛ በጀት እና የብር 5,008,432,852.43 ዋጋ ያላቸው የጤና ፕሮግራም መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ተከማችተው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ከመደበኛ በጀት የብር 109,565,947.68 ዋጋ ያላቸው እንዲሁም በጤና ፕሮግራም የብር 104,053,711.36 ዋጋ ያላቸው በድምሩ የብር 213,619,659.04 ዋጋ ያላቸው መድሃቶችና ህክምና መገልገያዎች ስድስት ወርና ከዛ በታች የመጠቀሚያ ጊዜ ያላቸው ናቸው፡፡ በስድስት ወሩ ውስጥ የብር 67,843,159.07 ዋጋ ያላቸው የመደበኛ በጀትና የብር 48,081,693.26 የጤና ፕሮግራም በድምሩ የብር 115,924,852.33 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው አልፎባቸዋል፡፡

የክትባት ሽግግር ስራ 93% ለማድረስ ታቅዶ 95% ደርሷል፡፡ የአሰራር ጥራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ለመስራት በሁሉም ቅርንጫፎች ያለውን የክትባት አያያዝና አስተዳደር ስርዓት የሚያሳይ የEVM ዳሰሳ ጥናት ተሰርቶ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት የማሻሻያ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI19:** የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች መጠየቂያና ሪፖርት ማድረጊያ የላኩ /RRF reporting rate/ - ወደ 95% ማድረስ፡- አፈጻጸሙ 83% ነው

KPI21: የክምችት ቆጠራ ትክክለኛነት (Inventroy accuracy rate) 100% ማድረስ- አፈጻጸም 80%፡፡

KPI22፡ የክምችት መገላበጥ በአማካይ በዓመት አሁን ካለበት ወደ 1.8 ማድረስ -- የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

KPI23፡ የጭነት ትዕዛዝ መጋዘን ደርሶ እስኪጫን ያለው አማካይ ግዜ (Order around time or warehouse order cycle time) ወደ 2 ሰዓት ማድረስ- አፈጻጸም 4 ሰዓት

KPI24፡ በዝቅተኛና ከፍተኛ መጠን መካከል የተከማቹ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች /Percentage of stock status observations in storage sites where pharmaceuticals stocked according to plan/

ለመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች መጋዘን ከገባበት አንስቶ ወደ ፋይናንስ ለማስተላለፍ የሚወስደው ቀን 3 ቀን ማድረስ- አፈጻጸም ከሀገር ውስጥ ገቢ ለሚደረገው መድሃኒቶች በ1.5 ቀን፣ ከውጪ ተገዝተው ለሚገቡ መድሃቶች 7.5 ቀን

### 3.4.6. የስርጭት እና ተሽከርካሪዎች ስምሪት አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር፤

ኤጀንሲው ለመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ስርጭት የሚጠቀምባቸውን ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ዘመናዊ ለማድረግና ለማሻሻል የሚያስችል የጂፒኤስ ተከላ በሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ስርጭት የሚወስደውን ጊዜ ለማሳጠር በታቀደው መሰረት መድሃኒቶችና የስርጭት ጊዜ ሲለካ በዋናው መስሪያ ቤት 9 ቀናት ይወስዳል፡፡ ይህም ቅርንጫፎች ከዋናው መስሪያ ቤት መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ጠይቀው አስፈላጊ ሂደቶች ተጠናቀው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች እስከሚሰራጭ ያለውን ጊዜ የሚለካ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት የብር 1,546,662,675.88 ዋጋ ያላቸው የመደበኛ በጀት እና የብር 12,221,793,673.96 ዋጋ ያላቸው የጤና ፕሮግራም በድምሩ የብር 13,768,456,349.84 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ስርጭት ተከናውኗል፡ ፡ የጤና ፕሮግራም ስርጭት ከፍ ያለው በነቀምት ቅርንጫፍ ውድ ዋጋ ያለው ለትኩረት ለሚሹ የቆላ በሽታዎች የተከናወነው የ532 ሚሊየን ብር ስርጭት ስለተካተተ ነው፡፡ መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የጤና ተቋማትን ፍላጎት በዓይነትና በመጠን በመለየት

ለ421 ሆስፒታሎች፣ ለ2,401 ጤና ጣቢያዎች፣ ለ892 ወረዳ ጤና ፅህፈት ቤቶችና ለ81 የዞን ጤና መምሪያዎች በየሁለት ወሩ በተቀናጀ መልክ በቀጥታ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI125:** ጤና ተቋማት ከቅርንጫፎች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካይ ጊዜ ወደ 1 ቀን መቀነስ - አፈፃፀሙ 1.5 ቀናት ነው፡፡

**KPI26፡** ቅርንጫፎች ከማዕከል መጋዘኖች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካይ ጊዜ ወደ 2 ቀን መቀነስ -አፈፃፀሙ 9 ቀናት ነው፡፡

**KPI27:** ጤና ተቋማት ድንገተኛ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብ ከጠየቁበት አገልግሎቱን ያገኙበት አማካይ ጊዜ (Average time from request to product dispatch) ወደ ግማሽ ቀን መቀነስ፣-- የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው

**KPI28:** የተሰበሰበ የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የስርጭት ርክክብ ማረጋገጫ ሰነድ /percentage of proof of delivery collected/- አፈጻጸም 80% ነው፡፡

## 3.5. ስ.ግ. አ.ግ. ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት

### *ስትራቴጂክ እርምጃዎች እና አፈጻጸማቸው*

### 3.5.1. የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ማጎልበት፤

የኤጀንሲው የሰው ሃይል ልማትን ለማጎልበት የሚያስችል የሶስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ እንዲሁም ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን የአተገባበር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI29:** የሰው ኃይል ፍልሰት ከ3.72% ወደ 3% መቀነስ፤አፈጻጸም 1.76%

**KPI30፡** ከኤጀንሲው ሰራተኞች ውስጥ 25% ያህሉን ግንባር ቀደም ማድረግ፤

### 3.5.2. የአቅርቦት ሰንሰለት መሠረተ ልማት ማጎልበት፤

የኤጀንሲው መጋዘኖች ወለላቸው ጥራት ለማስጠበቅ በውጪ ኮንትራክተር አማካኝነት የወለል ጥገና እየተከናወነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአዳማ፣ የባህር ዳርና የመቐለ ቅርንጫፎች የወለል ጥገና ስራ ተጠናቋል፡፡ GPS በሁሉም የጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ተገጥሟል፡፡ ትግበራውን ለማጠናከር የአሰራር መመሪያ ማሻሻያ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የ17 መጋዘኖች CCTV፣ Door Intrusion፣ Smoke Detection and Protection ተከላ በ8 ቅርንጫፎች ተጠናቋል፣ በ8 ቅርጫፎች ደግሞ የተከላ ስራው ተጀምሯል፡፡ የአዳማ ቅርንጫፍ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ማስወገጃ ኢንሲኔሬተር ግንባታና ተከላ ተጠናቆ የሙከራ ስራ ከተከናወነ በኋላ በአሁኑ ወቅት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡ ፡ የሐዋሳና ባህርዳር ቅርንጫፎች በቅርቡ ይጠናቀቃል የተቀሩት አምስት ቅርንጫፎች ደግሞ ግንባታቸው ተጀምሯል፡፡

የኤጀንሲዉ ዋና መስሪያ ቤት የG+7 የቢሮና የቀዝቃዛ ሰንሰለት የማጠናቀቂያ (Finishing) ግንባታ ስራ ግዥውን ለማከናወን ለሁለተኛ ግዜ በአለም አቀፍ የግዥ ዘዴ ጨረታው ጸድቆ የጨረታ ሰነዱ በመሸጥ ላይ ይገኛል፡፡

**የአፈጻጸም መለኪያዎች፡**

**KPI31**፡ የመጋዘን ቦታ አጠቃቀም ወደ 85% ማሳደግ --- በዋና መስሪያ ቤት 80% ደርሷል፡፡

**KPI32**፡ የጭነት መኪኖች አቅርቦት ወደ 100% ማሳደግ -- አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡

**KPI33**፡ የጭነት ተሽከርካሪዎች የስርጭት አገልግሎት የማይሰጡበት ጊዜ መጠን /Vehicle down time/ ወደ 14% መቀነስ-አፈፃፀሙም

### 3.5.3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ፈጠራን ማጎልበት፤

ኤጀንሲው የሚጠቀምበት የጤና ግብዓት መረጃ ስርዓት HCMIS ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመከታተል እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ፊቸሮች እንዲካተቱ አስፈላጊው ክትትል እየተደረገ ነው፡፡ የኤጀንሲውን ድረገጽ ለማልማት የኮንትራት ስምምነት ተፈርሟል፡፡

### 3.5.4. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጎልበት

የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፎች ተግባራዊ መደረግ ተጀምሯል። የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ለማጠናከር የአፈጻጸም መነሻ (baseline) መሰብሰቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ቅርንጫፎች ተበትኗል። እንዲሁም በአምስት ቅርንጫፎች ማለትም ሐዋሳ፣ አዳማ፣ ጂማ፣ ደሴ እና ድሬዳዋ ቅርንጫፎች ላይ የአፈጻጸም መነሻ ዳሰሳ ተሰርቷል። በዋናው መስሪያ ቤት የአውት ባውንድ ሎጂስቲክስ ዘርፍ የክምችትና መጋዘን አያያዝ እንዲሁም የስርጭትና ስምሪት አስተዳደር ክትትልና ትግበራ አፈጻጸም ለማጠናከር ክትትልና ድጋፍ ስራ እየተሰራ ነው። ቅርንጫፎች የክትትልና ግምገማ የአሰልጣኞች ስልጠናን ወደ ሁሉም ሰራተኞች እንዲያወርዱ ተደርጓል።

የድጋፋዊ ጉብኝት ዕቅድ እና ቼክሊስት ተዘጋጅቷል። በዕቅዱ መሰረት የድጋፋዊ ጉብኝት ቡድን ተቋቁሞ የስራ ቢጋር በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል። የተቀናጀ ድጋፋዊ ጉብኝቱ ሰሜንና ምዕራብ ሰሜን ክላስተር በሚገኙ ስድስት ቅርንጫፎች ላይ ተካሂዶ የድጋፋዊ ጉብኝቱ ሪፖርት ቀርቧል።

### 3.5.5. የመድሃኒት አቅርቦት ለማረጋገጥ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር

#### 3.5.5.1. የመልካም አስተዳደር እና ስነምግባር አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣

የኤጀንሲው መልካም አስተዳደር ዕቅድ የሴክተሩን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱን መሠረት በማድረግ ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፎች እንዲያዘጋጁ ተደርጓል።

የኤጀንሲው የዜጎች ቻርተር (የአልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ) ተዘጋጅቶ የዋናው መስሪያ ቤት የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ በ300 ኮፒ ታትሟል። ሁሉም የስራ ክፍሎችና ቅርንጫፎች የዜጎች ቻርተር (የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ) አዘጋጅተዋል።

የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ከማጠናከር አንጻር በመዝገብ ቅሬታ እንዲሰበሰብና ትንተና እንዲካሄድ ለማድረግ ታቅዶ ቅሬታዎቹ ተሰብስበዋል። የመልካም አስተዳደር ትግበራን በተመለከተ ቼክሊስት በማዘጋጀት የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ መረጃ የመሰብሰብና ማደራጀት ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

የካይዘን ፍልስፍና የሙከራ ትግበራ ለማስጀመር አራት ቅርንጫፎችና 6 ዳይሬክቶሬቶች ተለይተው በሃዋሳ፣ በመቐለና በአዲስ አባባ ቁጥር1 ቅርንጫፎችና በዋና መ/ቤት ላይ የነባራዊ

ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ተደርጓል። በዚሁ መሠረት በሃዋሳና በመቐለ ቅርንጫፎች የካይዘን ፍልስፍና ስልጠና ለ242 ሰራተኞች ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናው መሰረትም ትግበራው በሃዋሳና በመቐለ ቅርንጫፎች በይፋ ተጀምሯል። በቀጣይም በባህር ዳርና በጅማ ቅርንጫፎች ትግበራውን ለመጀመር የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

### 3.5.5.2. የህግ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣

ኤጀንሲው ለተከሰሰባቸው የውል ጉዳዮች መልስ በማቅረብ ክትትል የተደረገ ሲሆን ለኤጀንሲው የተወሰነው እንዲፈጸም ክትትል ተደርጓል። በአጠቃላይ በፍርድ ቤት የሚገኙ 7 የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፣ በወንጀል ጉዳይ በፖሊስና በዓቃቢ ህግ የሚገኙ 8 ጉዳዮች፣ አንድ በስራ ክርክር ፍርድ ቤት የሚገኙ ጉዳዮች አሉ:: በስራ ክርክር የነበሩ 3 ጎዳዮች ኤጀንሲው ላይ ተወስነዋል። በፍትሐ ብሔር ውሳኔ ከተሰጣቸው 3 ጉዳዮች ውስጥ 3ቱም ለኤጀንሲው የተወሰኑ ናቸው።

### 3.5.5.3. የህዝብ ግንኙነት ስራ ማጠናከር፣

የተለያዩ መልዕክቶችን በመቅረጽ በስቲከር፣ በባነርና በሮል አፕ ባነር በማሳተም እንዲሁም ከ17 በላይ ዜናዎችን በማዘጋጀት በየሁለት ሳምንቱ የውስጥ ጋዜጣ በማሳተምና በማሰራጨት፣ በተቋሙ የማህበራዊ ገጽ በመጫን፣ የሚዲያ ፎረም ወርክሾፕ በማካሄድ የማስተዋወቅ ስራዎች ተሰርተዋል። በነፃ የስልክ ጥሪ መስመር 111 ጥቆማዎች በመቀበል አግባብ የሆነ ምላሽ ተሰጥቷል። ከነዚህ ውስጥ 58 የመድኃኒት ዝርዝሮች ለማወቅ የተጠየቁ ናቸው፣ 10 ደግሞ በቆጠራ ምክንያት ተዘግቶ ስለነበር አገልግሎት መጀመሩን ለማወቅ፣ 39 መድኃኒት ፈልገው ስላጡና የተለያዩ መረጃዎችን ለማወቅ የደወሉ ናቸው።

የኤጀንሲው የኮሙንኬሽን ስትራቴጅ ተዘጋጅቷል። ተቋሙን አስመልክቶ የህብረተሰቡን እና የሰራተኛውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ የኮሙንኬሽን ስራዎች ተከናውነዋል። ከነዚህም ውስጥ በሁለት ቋንቋ የተዘጋጀ 1000 ኮፒ መጽሄት ታትሞ ለተለያዩ አካላት ተሰራጭተዋል፣ የኤጀንሲውን ስያሜና ሎጎ የማሳተምና የማስተዋወቅ ስራ፣ ኤጀንሲው ከያዛቸው ፍላግሽፕ ኢንሸቲቭ አንዱ የሆነውን "መድሃኒት የለም ይቁም" ("STOP STOCK OUT") የሚለውን መልዕክት በመቅረጽ ሁሉም ሰራተኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ እና ለተግባራዊነቱም ሁሉም ርብርብ እንዲደርግ 700 ስቲከር በማሳተም የማሰራጨትና የሞብላይዜሽን ስራዎች ተሰርተዋል፣ በ2010 በጀት ዓመታዊ የግምገማ መድረክ ላይ ኤጀንሲ ያከናወናቸው የተለያዩ

ስራዎች የሚያሳዩ ባነርና ሮላፕ ታትመው ለዕይታ ቀርበዋል፣ ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ጉዳዮች በማህበራዊ ሚዲያ ለማስተዋወቅ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ከ30 በላይ ዜናዎችን በማዘጋጀት በኤጀንሲው ማህበራዊ ድረ ገፅ ማሰራጨት ተችሏል። ኤጀንሲው መድኃኒቶች በአግባቡና በዘመናዊ መንገድ እንዲቃጠሉ ለማድረግ በ8 ቦታዎች እየተገነባ የሚገኘው ኢንሲኔሬተርን አስመልክቶ አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዲተላለፍ ተደርጓል፤ የቴሌቪዥን ዜና ሽፋንም እንዲያገኝ ተደርጓል።

ኤጀንሲው ትክክለኛ መጠሪያውን እንዲይዝ ለማድረግ ስያሜው የተቀየረ መሆኑን መነሻ በማድረግ አዲስ ሎጎ እንዲሠራ ተደርጓል።

የሰራተኞችን ተነሳሽነት ለመጨመር እና ኤጀንሲው እየሰራ ያሉትን ስራዎች እንዲያውቁ ለማድረግ በአዳማ ቅርንጫፍ እየተሰሩ ያሉትን ሰራተኛው እንዲጎበኝ ተደርጓል።

### 3.5.5.4. የጠቅላላ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር፣

ኤጀንሲው ያለበትን የተሽከርካሪ እጥረት ችግር ለመቅረፍ የኪራይ ተሽከርካሪዎች ግዢ ለማከናወን የጭነት አገልግሎት አወዳድሮ ግዥ ለማከናወን ጨረታው ተከፍቶ የዋጋ ምዘና በመከናወን ላይ ነው። እንዲሁም የተለያዩ መጠን ያላቸው ተሽከርካሪዎች በግልጽ ጨረታ ግዥ ለማከናወን አሸናፊ ተለይቶ የውል ስነድ ተዘጋጅቷል።

የ2010 በጀት ዓመት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በአግባቡ ተከናውኖ ለ2011 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉትን በመለየት የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቶ የግዥ ሂደት ተጀምሯል።

አገልግሎት የማይሰጡ የተሽከርካሪ መገልገያዎች ለማስወገድ የመለየት ስራ ተከናውኗል። በመጋዘኖች፣ ቢሮዎችና ሌሎች ጥገና የሚያስፈልጋቸው ስራዎች ከተለያዩ ስራ ክፍሎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች ጥገናው እንዲከናወን ተደርጓል።

የኤጀንሲው ንብረት የሆነ አንድ አይሱዙ እና ሶስት ፒክአፕ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜ ቆመው የነበረ ሲሆን በውስጥ አቅምና በካምፓኒ መሰራት የማይችሉትን በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በማወዳደር ከአሸናፊው ጋር ውል ተፈጽሞ በመጠገን ላይ ይገኛሉ።

### 3.5.5.5. ስርዓተ ጾታ እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ አገልግሎት ማጠናከር፣

ሴት ሰራተኞች ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት ለማምጣት ያሉ ማነቆዎችን በመለየት፣ በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ የአመራር ሰጭነት ላይ የሴቶችን ተሳትፎ በትምህርት ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እንዲቻል ከትምህርት ተቋሚት ጋር የግማሽ ክፍያና የነጻ የትምህርት ዕድል በማፈላለግ በዲግሪ እና በማስተርስ በጠቅላላው 115 ሰራተኞች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ኤጀንሲው ባከናወነው ጥናት መሰረት በኤጀንሲው በውሳኔ ሰጭነት ቦታ ላይ ያሉ የሴቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ የነበረ ሲሆን ኤጀንሲው የሴቶችን በውሳኔ ሰጪነት ቦታ ላይ ለማምጣት ሴቶችን ለማብቃት ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡ በዚህም በውሳኔ ሲጪነት ላይ ያሉ ሴቶች መጠን ከ9% ወደ 22.8% ደርሷል፡፡

በኤጀንሲው የወጣቶች ቀን ተከብሯል፡፡ በክብረ በዓሉ ላይ 37 ሰራተኞች የደም ልገሳ አድርገዋል፡፡ 470 ችግኞች ተተክለዋል፡፡

በኮልፌ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም ውስጥ ለሚገኙ ወላጅ አልባ ለሆኑ ህጻናት ብር 3710 የሚያወጣ የትምህርት መሳሪያና አንድ ኩንታል አልባሳት በቦታው በመገኘት ለ2011 የትምህርት ዘመን የሚሆን ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 4. የስድስት ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም፤

| ተ.ቁ. | የበጀቱ ርዕስ | ለስድስት ወር የተመደበ የገንዘብ መጠን (በብር) | በስድስት ወር ስራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን (በብር) | በስድስት ወር ስራ ላይ የዋለው የገንዘብ መጠን ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር (በ%) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ግዥ | 4,044,621,645 | 4,332,745,371.90 | 107 |
| 2 | የክምችት እና የስርጭት ወጪ | 41,631,788 | 66,663,264.31 | 160 |
| 3 | የንብረትና አገልግሎት ግዢ | 375,315,000 | 50,474,286.51 | 13 |
| 4 | አስተዳደራዊ ወጪ | 95,120,876.25 | 26,888,085.54 | 28 |
| 5 | የደመወዝና ትርፍ ሰዓት ወጪ | 104,694,948 | 78,825,782.79 | 75 |
| ጠቅላላ ድምር | | **4,661,384,257** | **4,555,596,791.05** | **98** |

## 5. በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ስራ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች

**ጠንካራ ጎኖች**

- የፕሌስመንት ጨረታ ምዘናና የኮንትራት ዝግጅት ሂደት መጠናቀቁ
- የክምችት ይዘት ሪፖርትና ትንተና በየወሩ እየተሠራ አስፈላጊ እርምጃዎች መወሰዳቸው
- ከአቅራቢዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ችግር ፈች ምክክሮች መደረጋቸው፣
- የፈጣን ለውጥ አምጪ ስልትን በመጠቀም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሆስፒታሎች ላይ የመድሃኒት አቅርቦት መሻሻሉ፣
- ዘመናዊ የተሽከርካሪ ስምሪት መቆጣጠሪያ መሳሪያ (GPS) በተሽከርካሪዎች ላይ መገጠሙ፣

**ደካማ ጎኖች/ያጋጠሙ ችግሮች**

- ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣
- የህይወት አድን መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት መቆራረጥ፣
- ከዋናው መስሪያ ቤት ወደተለያዩ ጤና ተቋማት ለሚላኩ መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ሞዴል-19 በወቅቱ አለመሰብሰቡ
- የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች ማስወገጃ ስርዓት አለመኖር
- የኤጀንሲው መጋዘኖች ወለል መፈራረስ፣

**የመፍትሔ እርምጃዎች**

- የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እጥረትን ለመቅረፍ የኤጀንሲውና የሴክተር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮችን ድጋፍ በማግኘት በተወሰነ መልኩ እንዲፈቀድ ተደርጓል፣
- ሞዴል 19 በወቅቱ ለመሰብሰብ ጥብቅ ክትትል እየተደረገ ይገኛል
- የማስወገጃ ማሽኖች /ኢንሲኒሬተሮችን/ በመገንባት ላይ ናቸው
- የመጋዘኖች ወለል ጥገና እየተከናወነ ነው

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

- የህይወት አድን መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን አቅርቦት ማሻሻል፤
- የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሻሻልና ዘመናዊ የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት፤
- ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ የሰራተኞች እርካታ ከፍ ማድረግ፣
- ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መዘርጋት /Enterprise Resource Planning/፤
- አቅራቢዎችን በመከታተል መድሃኒቶች በሚፈለጉበት ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ
- የሽረት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ማስወገድ

አባሪ 1፡ የቁልፍ አፈጻጸም መለኪያዎች (KPIs) ያሉበት ደረጃ ማጠቃለያ

| የKPI ቁጥር | የKPI ስም | የዓመቱ ዒላማ | የስድስት ወር አፈጻጸም | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| KPI1 | የጤና ተቋማት እርካታ | 80% | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI2 | የዱቤ ሽያጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሰብሰብ የሚወስደው ጊዜ | 60 ቀናት | | |
| KPI3 | ከአጋር ድርጅቶች ክፍያ ለመሰብሰብ የሚወስደው ጊዜ | 7 ቀናት | የግዢና አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ለመሰብሰብ 21 ቀናት በዓይነት ወደ መጋዘን ገብተው የክምችትና ስርጭት አገልግሎት ለሰጠናቸው ክፍያ ለመሰብሰብ 60 ቀናት ወስዷል | |
| KPI4 | ለመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ዋጋ ለመትከል የሚፈጀውጊዜ /Average Time from GRNF to Cost set date (IGRV-GRV) | 1 ቀን | 1 ቀን | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| KPI5 | የተገላባጭ ፈንድ የገንዘብ መጠንን መጨመር | በ10% | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI6 | በወቅቱ ሥራ ላይ የዋለና የተወራረደ የጤና ፕሮግራሞች ፈንድ | 100% | 100% | |
| KPI7 | Cash to cash cycle time (in months) | 12 ወር | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI8 | የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች የብክነት መጠን | ከ2% በታች | 0.65% | |
| KPI9 | የውስጥ አሰራርን በማሻሻል የተቀነሰ ወጪ | | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI10 | የፋይናንስ ሪፖርቶች ወቅታዊነት /Financial reporting timelines | 100% | 100% | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| KPI11 | የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ትንበያ ትክክለኛነት | ከ75% በላይ | በጤና ፕሮግራም 80.2%፣ በመደበኛ በጀት 66.1% | |
| KPI12 | የህይወት አድንና መሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት | 95% | የመደበኛ ህይወት አድንና መሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት 74.8%፣ የጤና ፕሮግራም 100% | |
| KPI13 | የግዢ ጥያቄ ከቀረበበት የግዥ ትዕዛዝ እስከሚይዝበት የሚወስደው ቀን | 90 ቀን | በቀጥታ ግዢ 91 ቀናት ሲሆን በግልጽ ጨረታ ደግሞ 107 ቀናት ይወስዳል | |
| KPI14 | የግዢ ትዕዛዝ ከያዘበት እስከ ኮንትራት የሚፈረምበት ያለውን ቀን | 15 ቀን | 27.6 ቀናት | |
| KPI15 | የግዥ ሂደት የሚወስደው ቀን | 160 | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI16 | ለመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዢ LC/CAD ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ወደብ ላይ እስከደረሰበት ያለውን ቀን /Supplier lead time variability/ | 90 ቀናት | በባህር ተጭነው ለሚመጡ 76 ቀናት፣ በአየር ተጭነው ለሚመጡ 83 ቀናት | |
| KPI17 | መድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዢ ወደብ ላይ ከደረሰበት | ከ25 ቀናት በታች | በባህር ተጭነው ለሚመጡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቀን አንስቶ ወደ ኤጀንሲው መጋዘኖች ገቢ እስከ ሚደረገው የሚፈጀው ቀን | | 48 ቀናት፣ በአየር ተጭነው ለሚመጡ 17 ቀናት | |
| KPI18 | አቅራቢዎች በውሉ መሰረት ማቅረብ የሚገባቸውን ያቀረቡበት መጠን /Supplier fill rate/ | | | |
| KPI19 | የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች መጠየቂያና ሪፖርት ማድረጊያ የላኩ /RRF reporting rate/ | 95% | 83% | |
| KPI21 | የክምችት ቆጠራ ትክክለኛነት (Inventroy accuracy rate) | 100% | 80% | |
| KPI22 | የክምችት መገላበጥ መጠን | 1.8 | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| | ለመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች መጋዘን ከገባበት አንስቶ ወደ ፋይናንስ ለማስተላለፍ የሚወስደው ቀን | 3 ቀናት | ከሀገር ውስጥ ገቢ ለሚደረገው መድሃቶች በ1.5 ቀን፣ ከውጪ ተገዝተው ለሚገቡ መድሃቶች 7.5 ቀን | |
| KPI23 | የጭነት ትዕዛዝ መጋዘን ደርሶ እስኪጫን ያለው አማካይ ግዜ (Order around time or warehouse order cycle time) | 2 ሰዓት | 4 ሰዓት | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| KPI24 | በዝቅተኛና ከፍተኛ መጠን መካከል የተከማቹ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች /Percentage of stock status observations in storage sites where pharmaceuticals stocked according to plan/ | 80% | | |
| KPI25 | ጤና ተቋማት ከቅርንጫፎች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካይ ጊዜ | 1 ቀን | 1.5 ቀን | |
| KPI26 | ቅርንጫፎች ከማዕከል መጋዘኖች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካይ ጊዜ | ወደ 2 ቀን | 9 ቀናት | |
| KPI27 | ጤና ተቋማት ድንገተኛ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብ ከጠየቁበት አገልግሎቱን ያገኙበት አማካይ ጊዜ (Average time from request to product dispatch | ግማሽ ቀን | | የሚለካው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ነው |
| KPI28 | የተሰበሰበ የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የስርጭት ርክክብ ማረጋገጫ ሰነድ /percentage of proofof delivery collected/ | 100% | 80% | |
| KPI29 | የሰው ኃይል ፍልሰት መጠን | 3% | 1.76% | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **KPI30** | ግንባር ቀደም ሰራተኞች፤ | 25% | | |
| **KPI31** | የመጋዘን ቦታ አጠቃቀም | 85% | 80% | |
| **KPI32** | የጭነት መኪኖች አቅርቦት | 100% | 100% | |
| **KPI33** | የጭነት ተሽከርካሪዎች የስርጭት አገልግሎት የማይሰጡበት ጊዜ መጠን /Vehicle down time/ | 14% | | |